## ለተግባራዊ ትምህርት የቪክቶሪያ ሰርቲፍኬት/ምስክር ወረቀት (VCAL) ምን ማለት ነው?

ይህ በቪክቶሪያ የተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት ለ11ኛ እኛ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች በፍላጎት የሚሰጥ እርዳታ ይሆናል።.

VCAL ከሥራ ጋር በተዛመደ እንዲለማመዱ ሲያደርግ፤ እንዲሁም ለኑሮ እና ለሥራ ጠቃሚ የሆነ ግላዊ የማንበብ፣ የመጻፍና የቁጥር ትምህርት ችሎታ ለማዳበር እድሉን ይከፍታል። እንደ ቪክቶሪያ የትምህርት ሰርቲፍኬት (VCE) የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬትም (VCAL) በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ብቃት ተቀባይነት ያገኘ ነው።

የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCAL) የሚወስዱ ተማሪዎች በተክኒካልና በበለጠ ትምህርት (TAFE) ላይ ለመሳተፍ፤ በሙያ ሰልጠና ለመውሰድ ወይም ትምህርት ቤት ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ሥራ የመግባት ፍላጎት ሊያሳድርባቸው ይችላል። ይሁን እንጂ የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCAL) ከጀመሩና ከዚያም የቪክቶሪያ ትምህርት ሰርቲፍኬትን (VCE) ለማካሄድ መወሰኑ ከዚያ በኋላ ቢሆንም ታዲያ የርስዎን ሀሳብ ለመቀየር ዘግይቷል ማለት አይደለም። እንደ የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCAL) አካል ሆኖ የሚያጠናቅቁት የቪክቶሪያ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCE) ክፍል ከአንዱ ሰርቲፍኬት ወደሌላው ለመተላለፍ ከወሰኑ በሚወስዱት የቪክቶሪያ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCE) ላይ ይቆጠራል። .

የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCAL) ተለዋዋጭ መሆን በርስዎ ፍላጎትና የመማር አስፈላጊነት በሚስማማ መልኩ የትምህርት ፕሮግራም ማካሄድ ይችላሉ። በሚከተሉት አራት ግዲታዊ ትምህርቶች ላይ ሙሉ ተቀባይነት ባገኘ አሰራርና አካላት ተመርጠዋል። :

- የማንበብና መጻፍ ችሎታ
- ከሥራ ጋር በተዛመደ ችሎታ
- በተለይ ለኢንዱስትሪ ሙያ ችሎታ
- ለግለሰብ መሻሻል ችሎታ

የርስዎን የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCAL) በጥሩ ሁኔታ ካጠናቀቁ ሰርቲፊኬት ይሰጥዎታል፤ እንዲሁም በምን የትምህርት ዓይነት እንዳጠናቀቁ የሚገልጽ የጽሁፍ ወረቀት ይደርስዎታል።

### ምን ማወቅ እንዳለብኝ

### ለቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCAL) ለምድ ነው የመረጥኩኝ?

በዩኒቨርስቲ ውስጥ በበለጠ ትምህርት (VCAL) ማካሄድ ለሚፈልጉ ተማሪዎች የቪክቶሪያ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCE) ጥሩ ምርጫ ቢሆንም ነገር ግን ለርስዎ ይህ ጥሩ እንዳልሆነ መስሎ ሊሰማዎት ይችላል።.

የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCAL) ተቀባይነት ያለው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ11ኛ እኛ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች በፍላጎት የሚሰጥ የሙያ ትምህርት ሲሆን እንዲሁም “ተግባራዊ ትምህርት” ተብሎ ይጠራል።

የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬትን (VCAL) ለማካሄድ ከመረጡ ተግባራዊ የሆነ ልምድ እና ‘ለሥራ ማስቀጠሪያ የሚሆን ሙያ’ ያገኛሉ፣ በተጨማሪም በሥራ ቦታ ወይም በቴፍ/ TAFE ገብቶ የበለጠ ስልጠና ለማካሄድ የሙያ ችሎታ ያገኙበታል።

## መቼ ነው VCAL ማካሄድ የምችለው?

በሞላው አስተዳደር ግዛት ውስጥ የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCAL)፤ የቴፍ/ TAFE ተቋማት እና ጥቂት የጎልማሳ ማህበረሰብ ትምህርት (ACE) ማእከላት ይቀርባሉ። በድረገፅ www.vcaa.vic.edu.au ላይ መጎብኘትና ትምህርት ቤቶችንና በሞላው የ VCAL አቅራቢዎች ዝርዝር ትምህርት በመፈለግ መምረጥ ይሆናል።

## የ VCAL ደረጃዎች ምንድ ናቸው?

VCAL ሶስት ደረጃዎች አሉት - መሰረታዊ፣ ማእከላዊና የበላይ ናቸው። እርስዎ የሚፈልጉትን ትክክለኛ ደረጃ በመምረጥ ለመወሰን አስተማሪዎ ወይም ባለሙያ አማካሪ ይረዳዎታል።

## ለመግባት የሚያስፈልግ ቅድመ ሁኔታዎች አሉን?

የለም። በርስዎ አቅም በሚስማማ የ VCAL ደረጃ ይጀምራሉ። ለርስዎ በጣም ተስማሚ በሆነ ደረጃ በመምረጥ ለመወሰን አስተማሪዎ ወይም ባለሙያ አማካሪ ሊረዳዎት ይችላል።

## የ VCALትምህርት ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል ?

የቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት ሰርቲፍኬት (VCAL) ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው። በመረጡት ደረጃ ላይ የ VCAL ፕሮግራም ትምህርት በሚገባ ካጠናቀቁ የ VCAL ሰርቲፍኬት እና ስለ ውጤቱ የሚገልጽ ጽሁፍ ወረቀት ማግኘት ይችላሉ። ብዙዎች ተማሪዎች የ VCAL ደረጃ ትምህርት በአንድ ዓመት ያጠናቅቃሉ።

## በጥሩ ውጤት የVCAL ካጠናቀቁ በኋላ ምን ያገኛሉ?

የ VCAL ፕሮግራም ትምህርትዎን በሚገባ ካጠናቀቁ በመረጡት የ VCAL ደረጃ ማለት የመሰረታዊ፣ የመካከለኛ ወይም የበላይ ደረጃ ተመርኩዞ ሰርቲፍኬት/ምስክር ወረቀት ያገኛሉ። በተጨማሪም ሁሉንም የVCAL፤ የVCE እና የሙያ ትምህርትና ስልጠና (VET) ክፍሎች ያዘለ የውጤት መግለጫ ጽሁፍ ወረቀት ያገኛሉ።.

## በእኔ VCAL ትምህርት ላይ ምን ይቆጠራል?

### የሙያ ትምህርትና ስልጠና (VET) ሰርቲፍኬት ምንድ ነው?

ተማሪዎች ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት፣ ማሰልጠኛ ተቋማትና በኢንዱስትሪ ላይ ተማሪዎች እንዲሰሩና ለሥራ ተቀጣሪነትና ለበለጠ ስልጠና እንዲዘጋጁ የሙያ ትምህርትና ስልጠና (VET) እድሉን ያቀርብላቸዋል። የሙያ ትምህርትና ስልጠና (VET) ኮርሶች በአብዛኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲቀርብ ይህም የ VCAL ትምህርትን በጥሩ ሁኔታ ሲጠናቀቅ በሃገር አቀፍ ተቀባይነት ባገኘ የሙያ ትምህርትና ስልጠና ላይ ለመግባት እንደ መረጃ ይቀርባል።.

## ከ VET ትምህርት በፊት የወሰድኩት በእኔ VCAL ላይ ይቆጠራልን?

አዎ። ቀደም ብለው የወሰዱት ትምህርት በርስዎ VCAL ላይ ምን ያህል እንደሚቆጠርና ለቀረዎት የ VCAL ፕሮግራም ደግሞ እቅድ ለማውጣት አስተማሪዎን ወይም የሙያ አማካሪን ማነጋገር አለብዎት።.

## የ VCE ትምህርት ዓይነት ወስጃለሁ። ታዲያ በማካሂደው VCAL ላይ ይቆጠራልን?

አዎ። የ VCE ክፍልን በጥሩ ሁኔታ ሰማጠናቀቅ ‘S/ያሚላ’ የሚል ውጤት ካገኙ በሚወስዱት VCAL ላይ ይቆጠራል። ስለቀሪው የ VCAL ፕሮግራም እቅድ ለማውጣት ከአስተማሪዎ ወይም ከባለሙያ አማካሪ ጋር መነጋገር አለብዎት።

## ሀሳቤን ከቀየርኩ ወደ VCE መለወጥ እችላለሁን?

አዎ። ሀሳብዎን ከቀየሩና ወደ VCE ለመለወጥ ከፈለጉ ወይም የ VCAL ፕሮግራምን ካጠናቀቁ በኋላ VCE ለመቀጠል ከፈለጉ፤ እንደ VCAL ክፍል ሆኖ በጥሩ ሁኔታ የተጠናቀቀ የሆነ VCE ክፍል በርስዎ VCE ላይ እንዳጠናቀቁት ይቆጠራል። እንዲሁም በርስዎ VCAL ውስጥ ያጠናቀቁት ሌሎች ክፍሎችና አካላት የተገኘ ነጥብ/ክረዲት ማስተላለፍ ይችሉ ይሆናል። ይህንን አማራጭ ስለመውሰድ ውሳኔ ከአስተማሪዎ ወይም ከባለሙያ አማካሪ ጋር መነጋገር አለብዎት።

## በ VCAL ሲመዘገቡ የፈረቃ-ጊዜ መሥራት እና/ወይም የሙያ ስልጠና መቀጠል እችላለሁን?

በ VCAL ትምህርት ሲመዘገቡ የፈረቃ-ጊዜ ሥራ ለማካሄድ ፍቃድ ማግኘት ይችላሉ። በዚህ ሥራ ውስጥ ሊካተት የሚችሉት:

- ከትምህርት ቤት በተዛመደ የሙያ ስልጠና ወይም ተግባራዊ ስልጠና/ traineeship
- የፈረቃ-ጊዜ ሥራ
- በሥራ ቦታ ላይ የታቀደ ለትምህርት ምደባ

## እንዴት VCAL ይገመገማል?

VCAL ተዋቅሮ የተሰራው ተቀባይነት ካገኙ ኮርሶች/ሰርቲፍኬቶች ነው። ለእያንዳንዱ ክፍል ባለው የፕሮግራም መመዘኛ ነጥብ ላይ ተመርኩዞ የርስዎ VCAL ፕሮግራም በአስተማሪዎ ይገመገማል።

## ለአጠቃላይ ስኬት ፈተና (GAT) ላይ መቀመጥ ይኖርብኛልን?

በጽህፈት፣ በሂሳብ፣ በሳይንስና በተክኖሎጂ፣ በሰብዓዊነትና ማሕበራዊ ሳይንስና ስነ-ጥበብ ትምህርት ያለን እውቀትና ችሎታ GAT የሚመዝን ፈተና ነው። ይህ አንድ ወይም የበለጠ VCE ክፍል 3 እና 4 በተከታታይ ለሚወስዱ ተማሪዎች በሞላ ይካሄዳል። የVCE VET ክፍል 3 እና 4 በተከታታል በማካሄድ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች በተጨማሪ በ GAT ፈተና ላይ መቀመጥ ይኖርባቸዋል። VCAL ክፍሎች ብቻ ለተመዘገቡ ተማሪዎች በ GAT ፈተና ላይ መቀመጥ አያስፈልግም። ይሁን እንጂ በበለጠ ወደ ትምህርት፣ ስልጠና ወይም ሥራ ለመግባት መሸጋገሪያ ጠቃሚ ከሆነ በ GAT ፈተና ላይ ለመቀመጥ መምረጥ ይችላሉ። ይሆናል።

## ምንድ ነው የምማረው?

ከርስዎ አስተማሪ ወይም የሙያ መማክርት እርዳታ ጋር በተለይ ለርስዎ በሚስማማና በሚፈልጉት ትምህርት የ VCAL ፕሮግራም ማቀናጀት ይችላሉ። ከዚህ በሚከተሉት አራት ግዴታዊ የሆኑ የ VCAL ዘለላ ላይ የክፍሎችና የአካላት ምርጫ ቀርቦልዎታል:

**ክፍል 1 - የማንበብ፣ መጻፍና የቁጥር ችሎታ**

በርስዎ VCAL ፕሮግራም ውስጥ መካተት ያለበት የማንበብና መጻፍ እንዲሁም የቁጥር የትምህርት ዓይነቶች ናቸው። ከ VCAL የማንበብና መጻፍ ችሎታ እና ከ VCAL የቁጥር ችሎታ ክፍሎች እና/ወይም ከ VCE እንግሊዝኛና ሂሳብ ወይም ከሌላ የሚመረጡ ጥናቶች እንደ በአጠቃላይ ትምህርት ሰርቲፍኬት (ለጎልማሶች) ውስጥ እነዚህ ሊመረጡ ይችላሉ።

**ክፍል 2 - በኢንዱስትሪ ያተኮረ ችሎታ**

በመካከለኛና በበላይ ትምህርት ደረጃ ያለ የርስዎ VCAL ፕሮግራም በሃገር አቀፍ ተቀባይነት ያለው የ VET ችሎታ ይዘትን ያካተተ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ ለሆነ አንድም የ VET ሰርቲፍኬት ማጠናቀቅ ወይም ማትኮር አይኖርብዎም። ለምሳሌ፡ የ VCAL ቅድመ ሁኔታን ለማሟላትና በብዙ የተለያየ ሙያ መስኮች ላይ ልምድ ለማግኘት ከተለያዩ የ VET ሰርቲፍኬቶች ላይ የተለያዩ የትምህርት ክፍሎችና አካላት ለመውሰድ ሊመርጡ ይችላሉ። የ VET አማራጭ መጠን ሰፋ ያለ ሲሆን፤ ለምሳሌ ያህል፤ አውቶሞቲብ፣ ኢንጂነሪንግ፣ የህንጻና ግንባታ ሥራ፣ መስተንግዶና ችርቻሮ፣ የብዙ መገናኛ ዘዴዎች፣ ኢንፎርሜሽን ተክኖሎጂ፣ እርሻ፣ የአትክልት ሥራ፣ የመጋዘን ሥራና በጸጉርና ውበት ሥራ።

**ክፍል 3 - ከሥራ ጋር በተዛመደ ችሎታ**

In order to develop '**የሥራ ተቀጣሪነትን**' **ችሎታ ለማዳበር ሲባል በ** VCAL **በኩል በሥራ ላይ የተመሰረተ ምደባ፣ ከትምህርት ቤት ጋር የተዛመደ የሙያ ሥራ/ስልጠና ወይም የፈረቃ-ጊዜ ሥራ እድል ምርጫዎች ይቀርቡልዎታል። እንዲሁም ለሥራ እንዲዘጋጁ የሚረዳ የትምህርት ክፍሎችን ማጥናት ሲችሉ፤ ለምሳሌ፡ የጤና ጥበቃና ደህንነት ሥራ ወይም የሥራ ቃለ-መጠይቅ ችሎታ ናቸው።** .

**ክፍል 4 - የግለሰብ እድገት ችሎት**

በርስዎ ማህበረሰብ ወይም በትምህርት ቤት ባሉ ፕሮጀክቶችና እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳትፎ ለማድረግ በርስዎ VCAL ፕሮግራም ውስጥ በማካተት፤ በቡድን አሰራር ችሎታ፣ በራስ መተማመንና ለህይወትዎና ለሥራዎ የሚጠቅም ሌላም ችሎታ እንዲያገኙ ይረዳል። ለምሳሌ፡ የመናፈሻ ቦታዎችን ለማጠናከር የርስዎ ትምህርት ቤት ከአካባቢ ምክር ቤት ጋር አብሮ ሊሠራ ይችላል። ከእንደዚህ ዓይነት ፕሮጀክት ጋ ለመማር የርስዎ መሳተፍ በሚያካሂዱት VCAL አስተዋጽኦ ሊያስገኝ ይችላል። .

## VCAL የት ሊያደርሰኝ ይችላል?

### የ VCAL ትምህርት በጥሩ ውጤት ካጠናቀኩ ወደ ከፍተኛ ትምህርት መግባት እችላለሁን?

ከትምህርት ቤት በቀጥታ ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመሄድ ካሰቡ ምናልባት VCAL ለርስዎ ጥሩ ምርጫ ላይሆን ይችላል። በቀጥታ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት ያቀዱ ተማሪዎች ብዙጊዜ VCE ያካሂዳሉ ታዲያ የአውስትራሊያ ሶስተኛ ደረጃ መግቢያ ማእረግ (ATAR) ከቪክቶሪያ ሶስተኛ ደረጃ መግቢያ ማእከል (VTAC) ማግኘት እንደሚችሉ ያደርጋል። በ VCAL የከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚማሩ ከሆነ እና ወደ ዩኒቨርሲቲ የመግባት ፍላጎት ካለዎት ታዲያ ተማሪዎች በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲ ፍቃድ ለማግኘት በ VCAL የከፍተኛ ደረጃ ያገኙት ሰርቲፍኬት ግምት ውስጥ ስለሚገባ ከርስዎ አስተማሪ ወይም የሙያ መማክርት ጋ ያረጋግጡ። ይሁን እንጂ ከትምህርት ቤት በቀጥታ ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት ብቻ አይደለም። አንዳንድ ሰዎች በቴፍ/ TAFE, የሙያ ትምህርት ሲማሩ፤ ይህም ወደ ዲፕሎማ ወይም

ድህረ-ዲፕሎማ ሊያመራቸው እንደሚችልና ከዚያም በዩኒቨርሲቲ ኮርስ ላይ ስለሚያገኙት ጥቅም ይወስናሉ።

## የVCAL ትምህርትን ካጠናቀኩ በኋላ የሚኖሩኝ ምርጫዎች ምንድ ናቸው ?

በቴፍ/ TAFE ተቋማትና ቀጣሪዎች ተቀባይነት ያለው ከሥራ ልምድ እና ችሎታ ጋር የተያያዘ በ VCAL ተግባራዊ ልምምድ ይቀርብልዎታል። ከትምህርት ቤት ወደ ሥራ፣ የሙያ ስልጠና ወይም ትሪኒሽፕ/ስልጠና እና/ወይም በቴፍ/ TAFE የበለጠ ስልጠና እንዲሄዱ ሁለቱም በጋር ይረድዎታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ለርስዎ የVCAL መሰረታዊ ደረጃ በ11ኛ ክፍል መማር ጀምረው በጥሩ ሁኔታ ካጠናቀቁ፤ በ12ኛ ክፍል VCAL የመካከለኛ ደረጃ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ገብተው እንዲያጠናቅቁ ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል። ወይንም የርስዎን ምርጫዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፤ ለዩኒቨርሲቲ ያቀረቡት ውሳኔ ትክክለኛ ምርጫ እንደሆነና ወደ VCE መዛወር ይሆናል።

## VCAL ወደ ሙያ ሥራ ለመግባት ዝግጁ እንድሆን ያደርገኛልን?

እንደ የእርስዎ VCAL ሰርቲፍኬት አካል ሆኖ የ VET ክፍሎችን ካጠናቀቁ ታዲያ ቀጣሪዎች ለሚሰጡት ከፍተኛ ግምት እውቀትንና ችሎታን ያዳብራሉ። ለምሳሌ፡ ለኢንዱስትሪ ማስተዋወቅ፣ በኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉትን እቃዎች መጠቀም፣ የጤና ጥበቃና ደህንነት ሥራ ናቸው። የ VET ክፍሎችን ማጠናቀቁ በዚህ ኢንዱስትሪ ውስጥ ለመሥራት ያለዎትን ፍላጎት ለቀጣሪው ለማስረዳት ይረዳል። .

ስለ VCAL የበለጠ ለማወቅ የቪክቶሪያ ስርአተ ትምህርትና ገምጋሚ ባለሥልጣን በስልክ 1800 134 197 ማነጋገር ወይም በድረገፅt [www.vcaa.vic.edu.au](http://www.vcaa.vic.edu.au) ላይ መጎብኘት